## የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮምሽን
## የብሔራዊ የጎርፍ ማስጠንቀቂያ ቁጥር 3
## ሰኔ, 2018


### 1. መግቢያ

ይህ የብሔራዊ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መልዕክት የመጪውን የክረምት ወቅት ማለትም እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ሴፐቴምበር 2026 (ከሰኔ 2018 እስከ መስከረም 2019 ዓ. ም.) ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ይሆናል፡፡ ይህ ወቅታዊ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው በቅርቡ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት በሰጠው የክረምት ወቅት አየር ጠባይ ትንበያ መሰረት ሲሆን በመጪው ወቅት መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያው ያካተታቸውን የጎርፍ ተጋላጭ የሆኑትን ቦታዎች ለቅፅፈታዊ ጎርፍና ለወንዝ ውሃ ሙላት ይበልጥ ተጠቂ የሆኑትን አካባቢዎች በመጠቆም ነው። በዚህ መነሻ መጪው የክረምት ወቅት በመጠንም ሆነ በስርጭት እንዲሁም በቦታ ሽፋን ዋነኛ የዝናብ ወቅት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ የክረምት ወቅት በተለያዩ አመታት የጉዳቱ መጠን ቢለያይም በአብዛኛው የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ አደጋ በመከሰት በህይወትና በንብረት ላይ የከፋ አደጋ እንደሚያደርስ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ምንም እንኳ መጪው 2018 ክረምት ኢ.ሊ.ኖ (El-Nino) ተፅዕኖ ስር ቢሆንም ተፅዕኖው በማይበረታባቸው አካባቢዎችና አልፎ አልፎ በሚከሰተው ከባድ ዝናብ ምክንያት በጎርፍ የሚጠቁ አካባቢዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በተለይም አልፎ አልፎ የሚኖረው የፀሃይ ሃይል ጠንካራ የደመና ክምችት እንዲኖር አጋዥ በመሆኑ በአጭር ሰዓታ የሚከሰተው ዝናብ ለቅፅበታዊ ጎርፍ ክስተት ምክንያት ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጎርፍ አደጋ ስጋት እንደሚኖር በወቅቱ በመገንዘብ የጉዳቱን መጠን ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ይህንን የጎርፍ ማስጠንቀቂያ ማዘጋጀት ከወዲሁ ለሚመለከታቸው አካላትና ማህበረሰቡ ዝግጅት እንዲያደርጉ ይረዳ ዘንድ ተገቢ ይሆናል፡፡

**በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት 2026 ክረምት ወቅት የተሰጠ ትንቢያ**

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ከተሰጠዉ የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትንበያ እንደሚያመለክተው ዋነኛ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች ያመዘነ እንዲሁም በመካከለኛውና በሰሜን ምዕራብ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚኖር ተመላክቷል፡፡

- በመሆኑም የክረምት 2018 ወቅቱ ዝናብ አገባቡ በደቡብምዕራብ ከመደበኛው ቀደም ብሎ እንደሚገባና በተቀረው የአገሪቱ ክፍል በመደበኛ ሁኔታ እንደሚገባ።
- በክረምቱ መግብያ በሰኔ ወር እና መውጫ በመስከረም ወር የዝናቡ ስርጭት የተዛባና ደረቅ ሰሞናት የሚዘወተርበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡
- አልፎ አልፎ የሚኖር የከባድ ዝናብ ክስተት ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በመካከለኛው፣ በምስራቅና በሰሜንምስራቅ የክረምቱ ዝናብ ቀደም ብሎ እንደሚወጣ፡፡
- በአንዳንድ የሀገሪቱ ውስን ኪስ ቦታዎች ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚኖር (አማራ፣ አፋር፣ ትግራይ)፣
- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የምዕራብ ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚሆን፡፡
- የሰሜን ሶማሌ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን፣ የደቡብ እና የምስራቅ ኦሮሚያ እና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልሎች በአመዛኙ መደበኛ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያ ተሰጥቷል።



## 2. ዓላማዎች

**የዚህ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ዋና ዓላማዎች፡-**

- **ቅድመ ጥንቃቄ ስራን ማስቻል** - በማህበረሰቡ እና በየደረጃው ባሉ መዋቅሮች አደጋው ከመከሰቱ በፊት አስፈላጊው የቅድመ ጥንቃቄ እንዲወስድ ያስችላል፡፡
- **የጉዳት ቅነሳ** - ጎርፉ ቢከሰት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ፡፡
- **ዝግጁነትን ማጎልበት** - ለአደጋው ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአደረጃጀት፣ የሎጂስቲክስና ቅንጅታዊ አሰራር ዝግጁነት እንዲኖር ያግዛል፡፡
- **አስቸኳይ ምላሽ ማመቻቸት** - በሁሉም ደረጃ በሚገኙ የአስተዳር መዋቅሮች ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የሚወሰዱ እርምጃዎችን አስቀድሞ ለማመቻቸት ይረዳል፡፡
- **መረጃ በወቅቱ ማድረስ** - መልዕክቱን ለሚመለከታቸው አካላት አስቀድሞ በማድረስ የመከላከልና የመቀነስ እርምጃዎች በወቅቱ እንዲወሰዱ ማስቻል፡፡
- **ቀጣይ ክትትል** - ከብሔራዊ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራ እና ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ትንበያ ጋር በማጣጣም ቀጣይ ክትትል ማድረግ፡፡

## 3. በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ከተሰጠዉ የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትንበያ እንደሚያመለክተው


- ➢ የክረምት 2018 ወቅቱ ዝናብ አገባቡ በደቡብ ምዕራብ ከመደበኛው ቀደም ብሎ እንደሚገባና በተቀረው የአገሪቱ ክፍል በመደበኛ ሁኔታ እንደሚገባ ፡፡
- ➢ በክረምቱ መግብያ በሰኔ ወር እና መውጫ በመስከረም ወር የዝናቡ ስርጭት የተዛባና ደረቅ ሰሞናት የሚዘወተርበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡
- ➢ አልፎ አልፎ የሚኖር የከባድ ዝናብ ክስተት ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ➢ በመካከለኛው፣ በምስራቅና በሰሜንምስራቅ የክረምቱ ዝናብ ቀደም ብሎ እንደሚወጣ፡፡
- ➢ የቤኒሻጉል ጉሙዝ፣ የምዕራብ ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ እና ደቡብምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚሆን፡፡
- ➢ የሰሜን ሶማሌ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን፣ የደቡብ እና የምስራቅ ኦሮሚያ እና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልሎች በአመዛኙ መደበኛ ዝናብ እንደሚያገኙ፡፡
- ➢ በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ ውስን ኪስ ቦታዎች (አማራ፣ አፋር፣ ትግራይ) ከመደበኛ በታች የዝናብ ስርጭት እንሚኖራቸው ትንበያ ተሰጥቷል፡፡

**ማስታወሻ፡ ለ2018 የክረምት ወቅት የተመረጡ ተመሳሳይ አመቶች 1997 እና 2023 እ.አ.አ ናቸው**

## 4. <u>የከባድ ዝናብና የጎርፍ ተጋላጭ ይሆናሉ ተብለው የተለዩ ቦታዎች</u>

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት የ2026 መኸር (ክረምት) ወቅት አየር ሁኔታ ትንቢያን እና የረጅም አመታት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በመኸር ወቅት የጎርፍ አደጋ ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች በየክልሉ በመለየት ዝርዝር ተሰርቷል፡፡

**Woredas at risk of flood hazard, June - Septemper, 2026**




በ2026 መኸር ወቅት ለጎርፍ ስጋት ይጋለጣሉ ተብሎ የተለዩ ወረዳዎችን የሚገልፅ ካርታ

**ሠንጠረዥ1፡ የጎርፍ አደጋ ስጋት ያለባቸውን ዝርዝር አካባቢዎች በየክልሉ**

| ክልል | ዞን | ወረዳ |
|---|---|---|
| ጋምቤላ | አኝዋክ | ጆር፣ አቦቦ፣ ጎግ፣ ጋምቤላ ዙሪያ እና ጋምቤላ ከተማ |
| | ኑዌር | ሁሉም ወረዳዎች |
| | ኢታንግ ልዩ ወረዳ | ኢታንግ ልዩ ወረዳ |
| አማራ | ደቡብ ጎንደር | ሊቦ ከመከም፣ አዲስ ዘመን ከተማ፣ ፎገራ እና ደራ ወረዳዎች |
| | ማዕከላዊ ጎንደር | ምስራቅ ደምቢያ፣ ጎንደር ዙሪያ እና አለፋ ወረዳዎች |
| | ምስራቅ ጎጃም | ደብረማረቆስ ዙሪያ እና ማቸከል ወረዳዎች |
| | ባህርዳር | ባህር ዳር ከተማ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ |
| | ምዕራብ ጎጃም | ሰሜን አቸፈር፣ ደቡብ አቸፈር |
| | አዊ | ዳንግላ |
| | ኦሮሞ ዞን | ከምሴ ከተማ፣ ዳዋ ጨፋ፣ ባቲ፣ ጨፋ ሮቢተ ከተማ፣ አርቱማ ፉርሲ እና ዳዋ ሃራዋ ወረዳዎች |
| | ሰሜን ሸዋ | አንፆኪያ፣ ኢፍራታ ግድም፣ ቀወት፣ አጣዬ ከተማ፣ ሸዋሮቢት ከተማ እና መራሀቤቴ ወረዳዎች |
| | ደቡብ ወሎ | ወረኢሉ፣ ደራ፣ ሀይቅ ከተማ፣ ለጋምቦ፣ ከምቦልቻ ከተማ፣ ደሴ ዙሪያ፣ መካነሰላም እና ቃሉ ወረዳዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | ሰሜን ወሎ | ላስታ፣ ዳህናን፣ ጉባላፍቶ፣ ወልድያ ከተማ፣ ሃብሩ እና መርሳ ከተማ |
| | ዋግኽምራ | ደህናን ወረዳ |
| ሶማሌ | ሲቲ | አፍደም፣ ኤረር፣ መኢሶ፣ ወረዳዎች |
| | ፋፌን | ጂግጂጋ ዙሪያ፣ ባብሌ፣ ጉርሱም፣ ቱሉጉሌድ፣ ወረዳዎች |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ደቡብ ኦሞ | ጂንካ ከተማ፣ ደቡብ አሪ ወረዳ |
| | ጋሞ | አርባምንጭ ዙሪያ፣ ገረሴ፣ ምዕራብ አባያ፣ አርባምንጭ ከተማ |
| | ወላይታ | አባላ አባያ፣ ሶዶ ከተማ፣ ዳሞት ሶሬ እና ጠበላ ከተማ |
| | ጌድኦ | ወናጎ እና ዲላ ዙሪያ |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ | ጊምቦ እና አዲዮ ወረዳዎች |
| | ቤንቺሽኮ | ደቡብ ቤንቺ ወረዳ ሚዛን አማን ከተማ |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል | ሃድያ | ሻሸጎ፣ አናሎሜ፣ ምስራቅ ባዳዋቾ እና ምዕራብ ባደዋቾ ወረዳዎች |
| | ሃላባ | ወይራ ዲጆ፣ አቶቴ ኢሉ፣ አላባ ቁሊቶ ከተማ እና ወይራ ወረዳዎች |
| | ከምባታ ጠንባሮ | ቃጫቢራ፣ ቃዲጋሜላ እና አዴሎ ወረዳዎች |
| | ስልጤ | ዳሎቻ፣ መራቤ ከተማ፣ ሳንኩራ፣ ሁልበርግ፣ ላንፋሮ፣ ስልጤ፣ ምስራቅ ስልጤ እና ሚቶ ወረዳዎች |
| | የም ልዩ ወረዳ | የም ልዩ ወረዳ |
| | ጉራጌ | ቸሃ፣ ኢዣ፣ ደቡብ ሶዶ እና ሶዶ አቦቴ ወረዳዎች |
| ኦሮሚያ | ምዕራብ ሸዋ | ኤጀሬና ወልመራ ወረዳዎች |
| | ደቡብ ምዕራብ ሸዋ | ኢሉ፣ ዳዌ፣ በቾ እና አለም ገና ወረዳዎች |
| | ፍንፍኔ ዙሪያ | ሰበታ አዋስ እና አቃቂ ወረዳዎች |
| | ምስራቅ ሸዋ | አቃቂ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ቦሰት፣ አዳማ፣ አዳማ ከተማ፣ አዳሜ ቱሉ ዲጆ ከምቦልቻ እና ቦራ ወረዳዎች |
| | ምዕራብ አርሲ | ሻላ፣ ኮፌሌ፣ ሲራሮ እና አርሲ ነገሌ ወረዳዎች |
| | አርሲ | መርቲ፣ ዝዋይ ዱግዳ፣ ሴሩ እና ጎለልቻ ወረዳዎች, |
| | ምዕራብ ሀረርጌ | ጉቢቦርደዴ፣ ኦዳቡልቱም፣ ጭሮ ዙሪያ፣ ጢሎ፣ ሃዊ ጉዲና፣ ቦኬ እና መኢሶ ወረዳዎች |
| | ምስራቅ ሀረርጌ | ጎሩ ሚቲ፣ አለማያ፣ ባቢሌ፣ ሜታ፣ እና ቀርሳ ወረዳዎች |
| | ጅማ | ኦሞናዳ፣ ሸቤሰምቦ፣ ሊሙሰቃ፣ ጊምቢ፣ ጎማ፣ ጌራ፣ ሰኮሩ፣ ሰንተማ እና ጂማ ከተማ |
| | ምስራቅ ወለጋ | ኪረሙ፣ ጊዳአያና፣ ናኖከምባ፣ ሲቡሲሬ፣ ሳሲጋ እና ጉቱጊዳ ወረዳዎች |
| | ምዕራብ ወለጋ | ጊምቢ ከተማ፣ ጊምቢ እና ሆማ ወረዳዎች |
| | ኢሉአባቦር | መቱ ዙሪያ፣ በደሌ ዙሪያ፣ ቡሬ እና ያዩ ወረዳዎች |
| | ምዕራብ ጉጂ | አባያ እና ገላና ወረዳዎች |
| አፋር | አውሲ(ዞን 1) | ዱበቲ፣ ዱብቲ ከተማ፣ አሳይታ፣ ሚሌ፣ ኤሊዳር፣ ሚሌ ከተማ፣ ጭፍራ፣ ገራኒ እና አፋምቦ ወረዳዎች፤ |
| | ጋቢ(ዞን 3) | አሚባራ፣ ወረር ከተማ፣ ቡሬ ሙዳይቱ፣ ዱለቻ፣ አዋሽ አርባ እና አዋሽ ወረዳዎች |
| | ኪልባቲ(ዞን 2) | አባኣላ፣ አባኣላ ከተማ እና ኮኔባ ወረዳዎች |
| | ፋንቲ(ዞን 4) | ያሎ፣ ጉሊና፣ አውራ፣ ቴሩ፣ ኢዋ እና መጋሌ ወረዳዎች |
| | ሃሪ(ዞን 5) | ዳሊፋጊ፣ ሃዲላላ፣ ተላላክ፣ ዳዌ፣ እና ስሚሮቢ ወረዳዎች |
| ሲዳማ | | ወንዶገነት፣ ቦርቻ፣ ብላቴ፣ ሎካ አባያ፣ ሃዋሳ ዙሪያ፣ ሃዋሳ ከተማ |
| ሐረሪ | | ሀረር ከተማ እና ገጠራማ ቀበሌዎች |
| ድሬ ዳዋ | | ድሬ ዳዋ ከተማ እና ገጠራማ ቀበሌዎች |

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | ምዕራባዊ ትግራይ | ታህታይ አዳያቦ፣ ፀለምት፣ ታህታይ ቀራሮወረዳዎች |
| | ደቡባዊ ትግራይ | ራያ አላማጣ፣ አላማታ ከተማ፣ ጨርጨር፣ ራያ አዘቦ፣ እንዳ መሆኒ እና ማይጨው ከተማ |
| | ማዕከላዊ | ላይላይ ማይጨው፣ ታህታይ ማይጨው ወረዳዎች |
| | ደቡብምስራቅ | ሀውዜን፣ ጋንታ አፋሾም፣ አፅቢወበረታ ወረዳዎች |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል | አሶሳ | አሶሳ ወረዳ፣ መንጊ፣ ባምባሲ እና አሶሳ ከተማ |
| አዲስ አባባ፡- | | የጎርፍ ተጋላጭ ወረዳዎች |

## 5. አጠቃላይ የመፍትሔ ሃሳብ-

የጎርፍ ስጋት ያለባቸው አካባቢዎች ጎርፍ ለሚያደርሰው አሉታዊ ተፅዕኖ የሚወሰዱ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ጉዳቱን ማቅለያ ተግባራት ላይ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አጋር ድርጅቶች የሚከተሉትን ቁልፍ መነሻ ስራዎች በስፋት እየተሰራበት ካለው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራዎች እንደአንድ ክፍል ተደርጎ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**ሠንጠረዥ2፡ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ ዝግጅት እና ምላሽ — የተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ሚና**

| ባለድርሻ አካል | የሚጠበቁ ቁልፍ ተግባራት (ቅድመ ማስጠንቀቂያ — ዝግጅት — ምላሽ — መከላከል) |
|---|---|
| **የክልል መንግስታት** | • የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መልዕክቶች ለህብረተሰቡ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማከናወን፤<br>• የክልል ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ጎርፍ ምላሽ ግብረ ሃይሎችን ወደ ስራ ማስገባት፡፡<br>• ከወረዳ ጽ/ቤቶች እና ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር ያለውን ቅንጅት በማጠናከር ዝግጅት ማድረግ፡፡<br>• የብሔራዊ ጎርፍ መጠባበቂያ እቅድን በመነሻ አድርገው የክልል እቅድ ማዘጋጀት፣ ተጋላጭ ህዝብን በቁጥር እና መለየት<br>• ከፌዴራል ጋር ቀጣይ መረጃ ልውውጥ ማድረግ<br>• የወንዞች ውሃ ከፍታ ክትትል ማድረግ<br>• አደጋው ቢፈጠር በአስቸኳይ ወደ ከፍተኛ ቦታ ማህበረሰቡን ማንቀሳቀስና በወቅቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ማቅረብ፤ |
| **የፌዴራል መንግስት ሴክተሮች** (ግብርና፣ ጤና፣ ውሃ እና ኢነርጂ፣ ንግድ እና ቀጠና ሚኒስቴር እና ሌሎች) | • የተቀናጀ ዘርፈ-ብዙ የጎርፍ መጠባበቂያና ምላሽ እቅድ ማዘጋጀት<br>• የወንዞች ውሃ ከፍታ ክትትል ማድረግ<br>• መዋቅራዊና መዋቅራዊ ያልሆኑ የጎርፍ መከላከያ ስራዎችን ማጠናከር<br>• ዘርፈ-ብዙ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>• ለተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና ከንጽህና ውሃ ጋር የተያያዙ በሽታዎችን ለመቀነስ የጤና ክትትል ማሻሻል እና አስፈላጊ ነገሮችን ዝግጁ ማድረግ<br>• የዉሃ ማጠራቀሚያ ኩሬዎችንና የዉሃ ጉድጓዶችን መጠገን፤<br>• እንስሳት በሽታ የመከላከል ለበሽታ እንዳይጋለጡ ክትባት መስጠት እና የመድሐኒት አቅርቦትን ከወዲሁ ማመቻቸት፣<br>• |

| | |
|---|---|
| **የሰብአዊ እና የልማት አጋሮች** | • ለጋራ እቅድ እና ዝግጅት ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ኮሚሽን፣ ሲክተሮች እና ከክልልች ግብረ ሃይል ጋር መተባበር። <br>• ከመንግስት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ቦታዎች ላይ በአስቀድሞ መተንበይ አሠራር መሠረት (Anticipatory Action) በጊዜ አስፈላጊ እርምጃዎች እና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ቦታዉ ላይ በማድረስ ማስቀማጥ <br>• አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የሚጠበቁ ድጋፍ ማድረግ። |
| **ሚዲያ** (ብሔራዊ እና ክልላዊ) | • ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ሴክተሮች እና ከክልል ቢሮዎች ጋር በመሆን የተረጋገጡ መረጃዎችን በተከታታይ ማሰራጨት፣ ፈጣንና ተደራሽ ማድረግ <br>• የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መልዕክቶች ለህብረተሰቡ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማከናወን፤ <br>• በውሃ ጥበቃ፣ በእንስሳት ሀብት እና ለሎች የግብርና ስራዎች አያያዝ ላይ ግንዛቤን ማሳደግ። <br>• የተሳሳተ እና ድንጋጤ ሊያስከትሉ የሚችሉ ያልተረጋገጡ መረጃዎችን ከማሰራጨት መቀጠብ። |
| **በተጎዱ አካባቢዎች ያሉ ማህበረሰብ** | • የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃን በጊዜው መከተል እና ለሌሎችም ማድረስ <br>• በአደጋ ጊዜ ወደ ከፍተኛ ቦታ መንቀሳቀስ ዝግጅት <br>• በውሃ ማቆር፣ ንጽህናና በሽታ መከላከል ስራዎች ተሳትፎ <br>• በጎርፍ መከላከያ ስራዎች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ <br>• ከደጋማ አካባቢ የሚኖረውን ወራጅ ውሃ መጠን ቀድሞ ማዋቅ እንዲቻልና ለሚወሰደው እርምጃ ዝግጅት ለማድረግ እንዲያስችል፣ በደጋማ ቦታዎች እና በዝቅተኛ አካባቢዎች ባለው ማህበረሰብ መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማመቻቸት፣ |

## 6. አጠቃላይ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች

- ከቀበሌ እስከ ብሔራዊ ደረጃ የተቀናጀ ቅንጅትና መረጃ ልውውጥ ማጠናከ፣
- በሁሉም ደረጃ ያሉ ተቋማት በቅንጅት በጋራና በተናጥል እቅድ የተመራ የአደጋ ስጋት መከላከያና ማቅለያ እርምጃዎችን ማጠናከር፣
- ተጋላጭ ማህበረሰቦችን በጊዜያዊነት ማሸሽ፣
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የአደረጃጀትና የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፣
- የቅፅበታዊ አደጋ ምላሽ ተግባራትን በአንድ የተቀናጀ ዘርፈ-ብዙ እቅድ ስር ማካተ፣
- የማህበረሰብ ተሳትፎና ግንዛቤ ማሳደግ የጎርፍ ጉዳትን መቀነስ።

<u>ማስታወሻ</u>፡- በቀጣይ የብሔራዊ የጎርፍ ስጋት ቅድመ ማስተንቀቂያ ግብረ ሃይል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት በሚሰጠው የአስር ቀን፣ የወር እና የወቅት አጋማሽ ትንበያ እና የረጅም አመታት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በ2026 የክረምት ወቅት የጎርፍ አደጋ ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች በየክልሉ በመለየትና በመከታተል ወቅታዊ መረጃ በመሰብሰብ ትኩረት ሰጥቶ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል።